# ታጠቅ

በአውሮፓ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማኅበር
የቴወሪ መጽሔት

ታህሣሥ 1961 ዓ.ም.

# ታጠቅ

በአውሮፓ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማኅበር
የቲወሪ መጽሔት

አዘጋጅ፦ ነገደ ጐበዜ
የዝግጅት አማካሪ፦ ፍቅሬ መርድ

ታኅሣሥ 1961 ዓ.ም. ዋጋው 1 ብር

ይዘት፡— ገጽ


| | |
|---|---|
| ርዕሰ—አንቀጽ | 1 |
| የዓለም ተማሪዎች ትግል | 5 |
| የመደብ ቅራኔና የነገድ ቅራኔ በኢትዮጵያ | 20 |
| ከሕዝቡ ጋር ተሰለፍ! ከሱ ተማር! አብረኸው ታገል! | 29 |


## ጠቃሚ አድራሻዎች፡—


በአውሮፓ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማኅበር

ፕሬዚዳንት፡— ግርማቸው ታደሰ
Karlsrogatan 15
Uppsala — SWEDEN

በሰሜን አሜሪካ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማኅበር

ፕሬዚዳንት፡— እንድርያስ እሼቴ
388 Orange St.
New Haven, Conn. 06511
U. S. A.

የትግላችን አዘጋጅ፡— አንዳርጋቸው አሰግድ
1 Berlin 19
Harbigstr. 1

የታጠቅ አዘጋጅ፡— ነገደ ጐበዜ
6183 Cité de Jazelles
Av. Jules Ferry
13 Aix-er- Provence
FRANCE


# ርዕሰ አንቀጽ

## «የማወቅ ዘመቻ»

እኛ ኢትዮጵያውያን ወጣቶች በሕዝባችን ላይ የተጫነውን የበደል ቀንበር ከየነውና ማጋለጥ ከጀመርን ብዙ ዓመታት አልፎናል።ለሕዝባችንም ችግሮች መፍትሄ የሚሆነው መሠረታዊ ለውጥ ብቻ መሆኑን በማመን ከሕዝቡ ጋር ባንድነት የሬቮሉሽናዊ ትግልን ጐዳና መርጠናል።ይህ አቋማችን «ባጋጣሚ» በአንዳንድ ወጣቶች ጉትጓችነትና በአንዳንድ ባለሥልጣኖች «ስህተትና ቸልተኝነት» እየተበረታታ እዚህ የደረሰ ሳይሆን የጊዜው ጭቆና ቀጥታና አስፈላጊ ውጤት ነው።የፊውዳሉ አቋም ፈርሶ ነፃ ኢትዮጵያ እስተምትመሠረትበት ጊዜ ድረስ፤ንቅናቄያችን እያደገ እንደሚሄድና በሃገራችን የነፃነት ትግል ውስጥ የግንባር ቀደምነት በታውን እንደሚይዝ ማንም ጥርጣሬ አይግባው።ወደድንም ጠላንም ይህ የታሪክ እርምጃ ውጤት ነው።ማንም ሊቋቋመው አይችልም።

«ዕድሜ ለመንግሥታችን» ከምንልበት ጊዜ ተነስተን ዛሬ «ዕድሜ ለኢትዮጵያ ሕዝብ» እስከልንበት ጊዜ ድረስ የተጓዝነው በጣም ረጅም መንገድ ነው።እንግዲህ ቆም ብለን የመጣንበትን መመልከትና ከሁሉም በላይ ደግሞ የምንጓዝበትን መንገድ ማስላሰል ያስፈልጋል።

የፊውዳሉን አቋም በውሳኔዎችና በስሜት ብቻ መኰነንና «ግፍ ነው» እያሉ ማማረር አልፈነው የሄድነው ደረጃ ነው።የኢትዮጵያ ሕዝብ ነፃነት የሚገኘው በመሠረታዊ ለውጥ ብቻ ነው ብለን ካመን ከትውልዳችንና ከተበዝባዡ የኢትዮጵያ ሕዝብ ገና ብዙ መራራ ትግልና መስዋዕትነት መጠየቁን መገንዘብ አለብን።እንግዲህ ድካማችንና መስዋዕትነታችን በከንቱ እንዳይሆን ካሁኑ ልንወስዳቸው የሚገቡን ብዙ እርምጃዎች አሉ።ከነዚህም አሁን በደረስንበት ታሪካዊ ደረጃ ታላቅ ቀዳሚነት ሊሰጠው የሚገባው ይህ «የማወቅ ዘመቻ»ያል ነው ትግል ነው።ማንን ለማወቅ? —ዓለምን፤አፍሪካን፤ኢትዮጵያን።

ዓለምን ሕዝብ ትግል፤የአፍሪካን ሕዝብ ትግል፤የኢትዮጵያን ሕዝብ ትግል።ዛሬ የሕዝባችን ትግል ከጠቅላላው የዓለም ሕዝብ ትግል የተለየ ነው ብሎ የሚያስብ፤የሃገራችን የወደፊት ዕድል ከአፍሪካ ዕድል የተለየ ነው ብሎ ራሱን የሚያታልል ወጣት ሁሉ ከፍለ ዘመን ተሳስቷል።

ይህ የምንለው «የማወቅ ዘመቻ» ግቡ የነገይቱ ኢትዮጵያችንን ከተማሩት አንጐል ወይም ከማንም ቢሮክራት ፕላን በወረቀት ላይ ነድፎ ለማውጣትና እንከን የሌላት ኢትዮጵያን ለመፍጠር አይደለም።በጠቅላላው ከኢትዮጵያ ሕዝብ ነፃ መውጣትና ዕድሉን እጁ ከማስገባት በስተቀር ከሁኑ ልናያቸው የምንችላቸው ጉዳዮች የተወሰኑ ናቸው።የነገይቱ ኢትዮጵያ የነፃው ሕዝብ ኢትዮጵያ ትሆናለች።በርግጥ የምናየው ይህንን ዕውነት ብቻ ነው።

ስለዚህ የማወቅ ዘመቻችን ተግባሩ ቁጭ ብሎ እንከን የለሽ ኢትዮጵያን ማፍተልተል ሳይሆን የሃገሪቱን የኢኮኖሚና ታሪካዊ አቋም አጥልቆ በመመራመር፤በሃገራችን የሚፋጩትን መደቦች ሥረ መሠረትና ትግሉ የፈለቀበትን ምክንያት አጠናቆ በማወቅና ከነዚህም ከቲኦሪና ከተግባር ከምናገኛቸው የተጨበጡ ዕውቀቶች የሬቮሉሽናዊ ትግላችንን መምርያና የሕዝባችንን ነፃ መውጫ ቍልፍ ፈልጐ ማሳየት ነው።ለዚህም እንግዲህ የዛሬው የሃገራችን ፊውዳል አቋም እንዴት እንደመጣ፤እንዴት እንዳደገና፤የግድ ደግሞ መጥፋቱ ስለማይቀር፤እንዴት እንደሚጠፋ ማየትና ማሳየት ይኖርብናል።የማወቅ ዘመቻችን ዋናው ግቡ ይህ ነው።

በዓለም ላይ ቆሞ የሚቀር ነገር የለም።የባርነት ዘመን እንዳለፈ ሁሉ የፊውዳሊዝምም ዘመን ያልፋል።ይህ የሁሉ ሕብረሰብ ታሪካዊ እርምጃ የሚከተለው የተፈጥሮ ሕግ ነው።ማንኛውም ሕብረሰብዊ አቋም ተወልዶ እስኪያልፍ ድረስ ሕይወት የሚሰጠውን ብቻ ሳይሆን ቆይቶም የሚያጠፋውን ዘር ባንድነት እንደያዘ ይኖራል።ባርነት ወደዓለም ሲመጣ አጥፊውን ባሪያን ይዞ ተወለደ።ፊውዳሊዝም ወደዓለም ሲመጣ አጥፊውን ገበሬን ይዞ ተወለደ።ካፒታሊዝም ወደዓለም ሲመጣ አጥፊውን ላብአደር ሠራተኛ ይዞ ተወለደ።ይህንን ዕውነት ካ



መንን የዛሬውን የፊውዳል አቋም የሚያጠፋው ዋና ኃይል ተበዝባዡ ላብአደር ገበሬ መሆኑን እናውቃለን፤እናያለንም።ትግላችንም ከላብ አደሩ ትግል ጋር የተዋሃደ ቢሆንም የተለየ የግንባር ቀደምትነት አደራ አለብን።

ይህን ስንል ምን ማለታችን ነው?ዛሬ በኢትዮጵያ የፊውዳሊዝምን አቋም አጥፊ ኃይሎች በየቦታው ብቅ ብቅ እያሉ መታየት ጀምረዋል።እርግጥ፤ማንኛውም የለውጥ ንቅናቄ መጀመሪያ ላይ የተበታተነ ነው።ይህ የተፈጥሮ ሕግ ነው፤ጭቆና ሲመረው ሁሉም በየተራ ይነሳል።ሁሉም ተራ በተራ በያለበት ይደመሰሳል።ስለዚህ ነው ዛሬ ሕዝቡ ደካማ መስሎ የሚታየው፤ለዚህ ነው ዛሬ ባላባቶቹ ኃይለኞች መስለው የሚታዩት።ነገር ግን ይህ ማንኛውም የለውጥ ንቅናቄ የሚያልፍበት የመጀመሪያው ደረጃ ነው። መጀመሪያ ሁሉም በያለበት፤ከዚያ ሁሉም ባንድነት።አንድነታችን ብቻ ነው የድላችን ዋስትና፤ይህ ብቻ ነው የማይበገር የለውጥ ሞተር።ዛሬ ተማሪ በያለበት ይጮሃል፤ሠራተኛ በያለበት ያጉረመርማል፤ገበሬ በያለበት ጭቆና በዛብኝ ይላል።ሁሉም በያለበት ሲከላከል ከፊቱ የተደቀነውን ጠላቱን እንጂ ዋናውን የሁሉም ጠላት የሆነውን የፊውዳል አቋም የሚያዩት ጥቂቶች ብቻ ናቸው።በመሃል ታዲያ ጨቋኞቹን በአንድነት አስተሳስሮ ኃይል የሰጣቸውና ተጨቋኞቹን ደግሞ በታትኖ የሚያዳክማቸው ሕብረሰባዊ አቋም ይረሳና በያለበት የማይጋፋት ባለጋራ ያጋጥማል።እኛ እንግዲህ ይህ የተጀመረው ትግል፤አንዳንዴ በባሕል፤በጐሣና በሃይማኖት እየተሳበበ ለጊዜው ያልተስተካከሉ ልዩ ልዩ መሥመሮችን ቢይዝም፤የትግሉ መሠረት የላብአደሩ ሕዝብ በጭቆና መንገፍገፍ መሆኑንና የነፃነታችንም ዋስትና ኢትዮጵያውያን ሁሉ በአንድነት ጭቆናን መቋቋማችን ብቻ መሆኑን ያለመሰልቸት ማስረዳት ይኖርብናል።እንዲያውም የተማሩት የሚጣልባቸው ዋናው የታሪክ አደራ ይህን የተበታተነ የለውጥ ኃይል ሰብስቦ በአንድነት ወደአንድ ግብ መምራት እንጂ የነፃነቱ ትግልማ ዋናው ኃይሉ ተበዝባዡ ላብአደር መሆኑንና ሕዝቡ ነፃ የሚወጣው በሕዝቡ በራሱ ብርታት መሆኑን መርሳት አይገባም።

ይህ የሃገራችን ጊዜያዊ ሁኔታ በቲኦሪ፤በፖለቲካና በድር

ጅት በኩል ከባድ የሆነ አደራ ይጥልብናል ። ለተጨቋኙ የኢትዮጵያ
ሕዝብ አንድነት ለመሥራት፤በግንባር ቀደምነት ይህን የአንድነት ጉዳና
መትለምና ማሳየት ያስፈልጋል።በጠቅላላው እያንዳንዱ ወጣት ኢትዮ
ጵያዊ ዛሬ ሕዝባችንንም ሆነ ዓለምን የሚመለከቱትን ችግሮች ከሌሎ
ች አጥልቆ በመመርመር፤ከሌሎች አስቀድሞ በማቅረብና ከሌሎች አስ
ቀድሞ ትክክለኛውን ዴሞክራሲያዊ መፍትሄ በማሳየት ግንባር ቀደም
ትነቱን ማስመስከር ይኖርበታል። ለዚህ ሁሉ እንግዲህ ስለ አገራችን
ጠቅላላ ጊዜያዊ ሁኔታ፤ስለሕዝቧ ታሪክና የኑሮ ዘዴያቸው፤ስለዓለም
ሕዝብ ትግል ያለንን ጠቅላላ ዕውቀት በይበልጥ ማደርጀት ያስፈልገና
ል። አሁን ባለንበት ታሪካዊ ወቅት የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማኅበራት
ቅድሚያ ሊሰጡት የሚገባው ይህ«የማወቅ ዘመቻ»ያልነው መሆን አ
ለበት የምንለው ስለዚህ ነው።በአሜሪካ የሚገኙት ወንድሞቻችን ይህ
ን ትክክለኛ እርምጃ መውሰድ ጀምረዋል፤የምንደሰትበት ነው።በአው
ሮፓም የጥናት ክበቦች በያለበት ተቋቁመዋል። ከእንግዲህ ወዲያ ዓ
መታዊ ጉባዔዎችም ዋና ተግባራቸው ውሳኔ ማሳለፍ ብቻ ሳይሆን ሰ
ፋፊ ጥናቶች ማቅረቢያና መለዋወጫ ሆነው፤የጥናት ጉባዔ መልክ መ
ያዝ አለባቸው።በየቦታው የሚደረጉትን ጥናቶች እያቀናበረና እያባዛ
የአንዱ ድካም ያፈራቸውን ዕውቀቶች ለሁሉም ማዳረስና በጠቅላላ
ው የወጣቶችን የፖለቲካ ንቃት ከፍ ማድረግ በተለይ የዓለም አቀፍ
ማኅበራችን ተግባር ሊሆን ይገባል።

እንግዲህ ይህ እንዲከናወን ከያንዳንዳችን መጠነኛ ድካ
ምን፤ሥራ ወዳድነትን፤መተባበርንና ዲሲፕሊንን ይጠይቃል።በሙሉ
ልባችን የመረጥነው የመሰረታዊ ለውጥ ጉዳና አለን።ለሚያስከትለው
መራራ ትግልና መስዋዕትነት የተሰናዳን ከሆንን ለረጅሙ ጉዟችን ብ
ርታትና ብርሃን ለሚሰጠን ለዚህ ለ«ማወቅ ዘመቻ»ከጊዜአችን ከፍለ
የማንወስንለት ምክንያት በፍጹም አይታየኝም።

«ታጠቅ»